# ምርቃት ለእናቴ

ዘጠኝ ወር አርግዘሽ አምጠሽ ወልደሽን፤
ማንም የማይቻለውን ህይወቴን ሰጠሽን፤
ተንከባክበሽ ይዘሽ ለፍተሽ አሳደግሽኝ፤
በትምህርት በፀባይ ኮትኩተሽ አነፅሽኝ፤
በትዕግስት በምክር መስመር አስያዝሽኝ፤
ስዋሽና ስቀጥፍ በሰዓቱ ቀጣሽኝ፤
ስበረታና ስጠነክር ተደሰትሽብኝ
ስደክምና ስለፈሰፈስ ደግፈሽ አቀምሽን፤
ጠግቤ ከእግዜር ስርቅ ጎትተሽ መለሽኝ፤
ስጨነቅ ስጠበብ ፀንተሽ አፀናሽ።

እናቴ ከአምላክ ያገኘኋት ስጦታዬ፤
እናቴ የማትረታዋ ጠበቃዬ፤
እናቴ የልብ አውቃ ጓደኛዬ፤
እናቴ ክፍያ የሌላት አገልጋዬ፤
እናቴ ሊሻኤ ነሽ መኩራዬ።

እናቴ አንቺ እንደምትመርቂኝ እኔ ልመርቅሽ፤
ለዋልሽልኝ ሁሉ እፁብ ድንቅ ተግባርሽ፤
የእናቶች ቀን ስለሆነ ዛሬ መታሰቢያ ቀንሽ።
እናቴ ወደር ለሌለው ፍቅርሽ እግዚአብሄር ይስጥሽ፤
ከክፉ ከልለሽ እንዳሳደግሽኝ አምላክ ከክፉ ይከልልሽ፤
ለአደረግሽልኝ በመሉ ፈጣሪ በመንግስቱ ይካስሽ፤
ለምትለምኛት ሁሉ ኪዳነ ምሕረት ትማለድሽ፤
በደስታሽና በችግርሽም ጊዜ ልጅዋ ክርስቶስ ይቁም ከአጠገብሽ፤
ሃያሉ አምላካችን ባለሽበት ደግፎ ይያዝሽ፤
ሰላም ጤናንና ፀጋን ያጎናፅፍሽ፤
የልብ ደስታንም ሰጥቶሽ ዘለአለማዊነትን ያውርስሽ፤
በቸሩ መድኃኔዓለም ይከፈል የምድሩ ውለታሽ።

ከ ኒኒ ለገሰ